# በኢፌዲሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

## የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

## የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

| ማውጫ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | ርዕስ | |
| 1 | መግቢያ | 2 |
| 2 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ | 2 |
| 3 | በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና | 3 |
| 4 | የዋና ዋና ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎን | 16 |
| 5 | ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች | 18 |
| 6 | የ2015 በጀት ዓመት የሰው ኃይል መግለጫ | 19 |
| 7 | የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈጻጸም | 20 |
| 8 | ማጠቃለያ | 21 |
| 9 | የ2015 በጀት ዓመት የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | 24 |

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ የውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) አግባብ የተከተለ ሲሆን ይህም ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲፈፅምና ተልዕኮው መሳካቱን እንዲያረጋግጥ የሚያግዝ ነው፡፡ ዕቅዱም ሲዘጋጅ መሰረት ያደረገው የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (2013-2017) መሰረት በማድረግ ፣የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማካተት ፣ የኢንስቲትዩቱን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚ ፣ ስጋትን በመተንተን ተዘጋጅቷል፡፡

በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱን ሶስት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ማለትም ጥናትና ምርምር፣ የላቀ አገልግሎት እና የአሰራር ስርዓትና የአቅም ግንባታ መሰረት በማድረግ እንዲሁም በአራቱ የአፈጻጸም ዕይታዎች መሰረት 11 ስትራቴጂያዊ ግቦችን በማካተት የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ተከልሶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

በዚሁ መሰረት በ2015 በጀት ዓመት ውስጥ የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማለትም መግቢያ፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች፣ በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት እቅድ አፈጻጸም ትንተና እንዲሁም በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች የተወሰዱ መፍትሄ እርምጃዎች እና ማጠቃለያ በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ

የኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለ አስራ አንድ ዓመታትን ያስቆጠረና በአፈጻጸም፣ በአደረጃጀት፣ በተጠሪነት እና በመሰረታዊ ስልጣንና ተግባር ረገድ ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑና ይህንንም በመቅረፍ በዘርፉ የሃገሪቱ ፍላጎት አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ እና ለሃገራዊ ልማት የሚ
ያበረክተውን ሚና በብቃት ለመወጣት በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የተደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በመከተል በዘርፉ የጥናትና የምርምር ተግባራት፣ የካሊብሬሽን፣ የቴክኒክ አገልግሎቶች፣ የስልጠና እና የማማከር ስራዎችን ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ በዓላማው ይህንን ታሳቢ በማድረግ ኢንስቲትዩቱ በማቋቋሚያ ደንብ የተሰጠውን ኃላፊነት እና ተግባር በአግባቡ ለመወጣትና በቀጣይ የታቀዱትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ተጠንቶ ለማጸደቅ በክትትል ሂደት ላይ ነው፡፡

የሰው ኃይል ግንባታን በተመለከተ በ Research Metedology, Change mgt ፣ እስታቲክስ፣ ምስልና ድምፅ ቅንብር፣ የሴት ሠራተኞች ፎረም የመረጃ ነፃነት ህግና ተያያዥ ጉዳዮች፣ training on integrazation፣ EGP እና በሌሎችም በጠቅላላ ድምር ወ= 159 ሴ= 102 በድምሩ ለ261 ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በISO 19011 የጥራት ስራ

አመራር ኦዲት ለ50 ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ለድህረ ምረቃ ት/ቤት የመግቢያ ፈተና ላለፉ 3(ወ=2 ለሁለተኛ ዲግሪ, ሴ=1 ለሶስተኛ ዲግሪ) ሠራተኞች የት/ት ዕድል ተሰጥቷል።

የኦዲት ስራዎች በተመለከተ ሶስት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እና አንድ በተሽከርካሪ ስምሪት ዙሪያ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል። የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች ከመዘርጋት አኳያ በዜጎች ቻርተር መሠረት አገልግሎት መሰጠቱን የትንተና ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን በደንበኞች ዙሪያ በካሊብሬሽን ቀጠሮ መዘግየት ጋር ተያይዘው የተነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ለማሻሻል ስምምነት ላይ ተደርሷል። በተጨማሪም ለተገልጋዮች የቅሬታ እና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርአት ተግባራዊነቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በቀጣይም ደንበኞች በቀጥታ ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት 4 ዲጂት ነጻ የስልክ መስመር ለመዘርጋት እየተሰራ ይገኛል።

## 3. በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና

አጠቃላይ የኢንስቲትዩቱ የ2015 በጀት ዓመት የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም 82 ሲሆን በዝርዝር ሲታይ የተገልጋይ ዕይታ አፈጻጸም 90.4%፣ የፋይናንስ ዕይታ 93%፣ የውስጥ አሰራር ዕይታ 70% እና የመማርና እድገት እይታ 76.5% ነው።

### ግብ 1፡ የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ (ክንዉን 89%)

### 1.1. ጥናትና ምርምር ማካሄድ (ክንዉን 91.6%)

1.1.1 አራት ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ታቅዶ፡-

- በህክምና መሳሪያዎች "Testing እና Verification" ላይ፤
- በተመረጡ የጨርቃጨርቅና ቆዳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ላይ የተመጣጠነ ሚዛን ማስተካከያ ውጤት ወጥነት እና አስተማማኝነት ላይ ፤
- 'Potentiometric Method' በመጠቀም የ 'Resistance' ልኬት ትክክለኛነት የማሻሻል ሥራ ጥናቱ የተጠናቀቀ ሲሆን
- የክትባት መድኃኒቶች ማቆያ ፍሪጅ በማሻሻል ፕሮቶታይፕ ለማምረት ኘሮፖዛል የተዘጋጀ ቢሆንም የማምረት ሥራውን ለማከናወን ዲሲ ኮምኘሬሰር በአገር ውስጥ ባለመገኘቱ ጨረታ ወጥቶ በሂደት ላይ ነው **(ክንዉን 91.6%)።**

### 1.2. የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 86.5%) ።

1.2.1 ለ31065 የካሊብሬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በዋናው መ/ቤት 24752 እንዲሁም በቅርንጫፍ ላብራቶሮች 2121 በድምሩ 26873 የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል (ክንውን 86.5%)። አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በሰሜኑ ክፍል ከጸጥታ ጋር በተያያዙ ችግሮች የተፈለገዉን ያህል እንቅስቃሴ ባለመደረጉ ነዉ።

## 1.3 የጥገና አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 84%)

1.3.1.ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ ለ300 ሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ252 መሳሪያዎች አገልግሎቱ ተሰጥቷል (ክንውኑ 84%)፡፡

## 1.4 የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 100%)

1.4.1 በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ሙያዊ ስልጠና መስጠት ታቅዶ

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

- ለ9 ለአንሊሚትድ ፓኬጅንግ ድርጅት የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የጽንሰ ሃሳብና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ለ25(ወ=5 ሴ=20) ወንዶች የናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ድርጅት ባለሙያዎች በአይ ኤስ ኦ (ISO)17025፡2017 የላቦራቶር ጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ላይ የጽንሰ ሃሳብ ስልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡
- ለ 8 ወንድ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች በግዝፈትና ግፊት አለካክ መስኮች ስልጠና፣
- እንዲሁም 5 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለሙያዎች አጠቃላይ በሥነ-ልክና እርግጠኛ ያለ-መሆን ጽንሰ ሀሳብ፣ በርዝመት፣በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በግፊት፣ በይዘት፣ በሚዛንና ኃይል መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን፣ እንዲሁም የመለኪያ መሳሪያዎች አያያዝና ደህንነት አጠባበቅ ላይ ሥልጠና ተሰቷቸዋል (ክንውን 100%)፡፡

**በሳይንስ መሳርያዎች ዘርፍ**

- በአናሎግ ኤሌክትሮኒክስ የዲዛይንና የብልሽት ፍለጋ (Design and troubleshooting) ላይ ለ15 (ወ=11,ሴ=4) ከህብረተስብ ጤና ኢንስቲትዩት ለተላኩ የባዮሜዲካል ምህንድስና ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ተግባራዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በዲጂታል ኤሌክትሮኒክስ የዲዛይንና የብልሽት ፍለጋ (Design and troubleshooting) ላይ ለ14 (ወ=10,ሴ=4) ከህብረተስብ ጤና ኢንስቲትዩት ለተላኩ የባዮሜዲካል ምህንድስና ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ተግባራዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ለኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን በተፈረመው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት በሳይንስ መሳሪያዎች አገልግሎቶችና ቴክኒካዊ ሥራዎች እና ህክምና መሳሪያዎች "Toubleshooting" ላይ በሁለት ዙር ( በመጀመሪያው ዙር ለ 22 ወንዶችና 9 ሴቶች በሁለተኛው ዙር ለ 24 (13 ወንዶችና 11 ሴቶች ) ስልጠና በድምሩ ለ66 ባለሙያዎች በአዳማ ከተማ ተስጥቷል (ክንውን 100%) ፡፡

## 1.5 የምክር አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 100%)

1.5.1 በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች 100% የምክር አገለግሎቶች ለመስጠት ታቅዶ

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

- ለመተሓራ ስኳር ፋብሪካ ስለ ነዳጅ ማከማቻዎች ስለ ልኬት የመትነንን ባህሪ ስላላቸው ፈሳሾች የልኬትና የአያያዝ ደረጃዎች ፣የነዳጅ ጥራት መመርመሪያዎች ላይ ሙያዊ ድጋፍ በተጠየቀው መሠረት ተሰጥቷቸዋል፣
- ለኦሮሚያ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን በሙቀት ስነልክ ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ተሰቷል (ክንውን 100%) ፡፡

**በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ**

- በጥራት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት በአለም ባንክ ብድር ተገዝተው ለገቡ 273 የተለያዩ መሳሪያዎች በአምራቹ ስፔሲፊኬሽን መሰረት ለመቅረባቸው የፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡ ሪፖርትም ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተላልፏል፡፡
- ከኦሮሚያ የግብርና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለሥልጣን የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ግዢ የቴክኒካል ስፔሲፊኬሽን ጥናትና ዝግጅት ላይ የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡
- ከኦሮሚያ የግብርና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለሥልጣን የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ግዢ የቴክኒካል ግምገማ ላይ የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል (ክንውን 100%) ፡፡

## 1.6. የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 65.4%)

1.6.1. ለ26 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ጥገናና ኮሚሽኒንግ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ17 ደንበኞች መስጠት ተችሏል (ክንውን 65.4%)፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በታቀደው መሰረት ከደንበኛ ጥያቄ ባለመቅረቡ ነው፡፡

## 1.7. የተጠቃሚ እርካታ መመዘን (ክንውን 100%)

1.7.1 የደንበኞች እርካታ ላይ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡ የእርካታው መጠን 72% ሆኗል (ክንውን 100%)፡፡

## ግብ 2፡ ተደራሽነትን ማሳደግ (ክንውን 93%)

## 2.1 በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ አዳዲስ አገልግሎት መስጠት (ክንውን 100%)

2.1.1 በኤሌክትሪካል አለካክ መስክ በተንቀሳቃሽ ላብራቶር የካሊብሬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ የመልቲፈንክሽናል ካሊብሬተር እና የኢነርጂ ሜትር በመጠቀም በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ የካሊብሬሽን አገልግሎት ተጀምሯል (ክንውን 100%)፡፡

2.2 **በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋት**(ክንውን 80%)፡፡

2.2.1 በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ (Thermometers, Moisture) መስክ ካሊብሬሽን ለመጀመር ታቅዶ ስልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 80%)፡፡

**2.3 የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 100%)

2.3.1. **የሳይንስ መሳሪያዎች** የጥገና ወርክሾኘ እና የመለኪያ መሳሪያዎች የካሊብሬሽን ላቦራቶሪ ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብቶች፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ፡-

**በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ**

- የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የላብራቶሪ መሳሪያዎች **ካሊብሬሽን እና** ጥገና ተቋማዊ ማዕከል ለማቋቋም እንዲያስችላቸው አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችና ፋሲሊቲዎች ተጠንተው እንዲዘጋጁላቸው በጠየቁት መሰረት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

- ለኦሮሚያ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን በሙቀት የመስክ ካሊብሬሽን ላይ የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ሰልጠና ተሰጥቷል፣
- ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፒራዝ ለመለኪያ መሣሪያዎች ግዥ የቀረቡ ጨረታዎች የቴክኒክ ግምገማ ሪፖርት ላይ የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ተሰቷል፣
- እንዲሁም አዲስ ለሚገዙ seed purity moisture and germination laboratory በአጠቃላይ ወደ 43 አይነት የተለያዩ የላብራቶሪ ዕቃዎች technical specification ዝግጅት አገልግሎት ድጋፍ ተሰቷል፣
- ለኢትዮጵያ አክርድቴሽን አገልግሎት የጥራት ኦዲት ቴክኒካል ገምጋሚዎች /Technical Assessors/ የተግባር ስልጠና ሲሰጣቸው የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡
- ለኦሮሚያ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን እና ለኦሮሚያ አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በላቦራቶር የጥራት ሥራ አመራር /ISO/IEC 17025/ ሰነድ አዘገጃጀት ላይ የቴክኒክ ደጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡
- ለአማራ ክልል የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የውስጥ ካሊብሬሽን ላቦራቶር ማቋቋም የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል (ክንውን 100%)፡፡

2.4 **የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆን ማድረግ** (ክንውን 100%)

2.4.1 ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ለማዘጋጀትና ለመጫን ታቅዶ የተለያዩ ዜናዎች እና በኢንስቲትዩቱ የተከናወኑ ኩነቶች በመ/ቤቱ ዌብ ሳይት ላይ ተጭነዋል (ክንውን 100%)፡፡

**2.5. የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት** (ክንውን 100%) ፡፡

2.5.1 በተመረጡ 3 አካባቢዎች እናበዩኒቨርስቲዎች የግንዛቤማስጨበጫ ለመስጠት ታቅዶ

- ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ከሀረሪ ክልል፣ ከሶማሊያ ክልል እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ከምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ ዞኖች ለተውጣጡ ለ95(ወ=68 ሴ=27) የሥራ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በሀረር ከተማ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከአሜሪካ የኢትዮጵያ ጤና ዘርፍ አገልግሎት ጥራት ማሻሻያ ድጋፍ ፕሮጀክት (USP PQM+) ጋር በመተባበር ከጤና ተቋማት ለተውጣጡ (ወ180 ፣ሴ=191) በድምሩ ለ371 የጤና ባለሙያዎች በአዳማ፣ ጐንደር፣ ጂማ፣ ድሬዳዋ፣ ደሴ እና ሃዋሳ ከተሞች በአለካከ መስከ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም** ውጤታማነትን ማሳደግ (ክንውን 98%)፡፡

3.1. የበጀት አጠቃቀምን መከታተል (ክንውን 89.4%)

3.1.1. የፀደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት ለመጠቀም ታቅዶ በ2015 በጀት ዓመት የዓመቱ አፈጻጸም 89.4% ሆኗል (ክንውን 89.4%)፡፡

**3.2. የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ** (ክንውን 97.5%)

3.2.1. በበጀት ዓመቱ 12,000,000 የአገልግሎት ገቢ መሰብሰብ እና የተሰበሰበውን የአገልግሎት ገቢ ለገ/ሚ/ር ፈሰስ ለማድረግ ታቅዶ የካሊብሬሽን፣ የጥገና፣የምክርና የስልጠና ገቢዎች ከሐምሌ ወር 2014 እስከ ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ብር 11,699,973.53 ተሰብስቧል (ክንውኑ 97.5%)፡፡

**3.3. የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** (ክንውን 100%)፡፡

3.3.1 በ5 የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እና አንድ የክዋኔ ኦዲት ለማዘጋጀት ታቅዶ የ2014 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ፣የ2014 በጀት ዓመት 4ኛ ሩብ ዓመት፤ የ2015 በጀት ዓመት የ1ኛ፣ 2ኛ፣3ኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት፣ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር እና ለገንዘብ ሚ/ር በተሰጡ አስተያየቶች ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ሪፖርት እና የሥጋት አካባቢን በመለየት በተሽከርካሪ ስምሪት ዙሪያ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 4. የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት** (ክንውን 50%)፡፡

**4.1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ** (ክንውን 50%)፡፡

**4.1.1** 1 ኘሮጀክት በማዘጋጀት ድጋፍ ለማፈላለግ ታቅዶ ከውጭ አጋሮች ጋር በመነጋገር የሰራተኞች የትራንስፖርት ሰርቪስ ተጠይቶ በሂደት ላይ ነው (ክንውን 50%)፡፡

**ግብ 5 አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** (ክንውን 80.%)

**5.1. ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት** (ክንውን 70.4%)

5.1.1. በዳይሜንሽናል፣ በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካልና በግፊት የአለካክ መስኮች ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን አለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለመጠበቅ ታቅዶ በግዝፈት፣በኤሌክትሪካልና በወበቅ የመጀመሪያ ደረጃ ብሔራዊ የማነጻጸሪያ ስታንዳርዶች እና የግፊት ሁለተኛ ደረጃ ምድብ የማነጻጸሪያ ስታንዳርዶች በደቡብ አፍሪካ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል፡፡

- የዳይሜንሽናል እና የግፊት የመጀመሪያ ደረጃ ብሔራዊ ስታንዳርዶች በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ድጋፍ በጀርመን የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ለማስደረግ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም፣ የጥመልፕ የላከውን የውል ስምምነት በበጀርመን የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ምንም እንቅስቃሴ የለም (ክንውን 50%)፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት 'በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የዳይሜንሽናል እና የግፊት የመጀመሪያ ደረጃ ብሔራዊ ስታንዳርዶች/ኢታሎኖች/ የዕርከን ተዋረድ ትስስር የመጠበቂያ ጊዜያቸው ካለፈባቸው ወደ አምስት ዓመት እየተቃረበ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ከ 12 ዓመት በላይ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው አገልግሎት ይሰጥ የነበረው የግፊት አለካክ መስክ በተለይ የአየር ግፊት መለኪያ መሳሪያዎች የልኬት አገልግሎት ለማቋረጥ አስገዳጅ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት የውጭ ምንዛሪ ድጋፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለማስጠበቅ በሂደት ላይ ነው፡፡ '

5.1.2. 211 ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለማሰራጨት ታቅዶ 'በዋናው መስሪያ ቤት እና በደንበኞች የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች የሚገኝ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች፡-

- በ ግዝፈት ሥነ-ልክ ላቦራቶሪ 140 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተከናውኗል፡፡
- በኤሌክትሪካል፣ ጊዜና ድግግሞሽ ሥነ-ልክ ላቦራቶር የ Trans volt, and 14 fixed value standard resistance from 0.001 ohm to 1 mega ohm calibration ተከናውኗል፡፡
- በሙቀት ሥነ-ልክ ላቦራቶር PRT=24፤Theromoucople=12፣Bath characterization=5 እና መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል፡፡
- በግፊት ሥነ-ልክ ላቦራቶር ለ13 የሁለተኛ ምድብ የማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል፡፡
- በግፊት ሥነ-ልክ ላቦራቶር ለ10 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል፡፡ በአጠቃላይ 214 የመለኪያ መሳሪያዎች የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል (ክንውን 101%) ፡፡

## 5.2. ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል (ክንውን 100%)፡፡

5.2.1. 5 (በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በይዘት እና ሚዛን) ዓለም አቀፍ ዕውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች ማስቀጠል በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ መውሰድ እና ማስተካከያዎችን ለማከናወን ታቅዶ በሁሉም ዓለም አቀፍ ዕውቅና ባላቸው የአለካክ መስኮች ዓመታዊ የውስጥ ጥራት ኦዲት ተከናውኖ የእርምት እርምጃ ተወስዷል (ክንውን 100%)፡፡

5.2.2. ዕዉቅና ባልተገኘባቸው 6 የአለካክ መስኮች (በዳይሜንሽናል፣ በሀይል፣ ይዘት(ላርጅ ቮልዩም)፣በቶርክ፣ በሀርድነስ፣ በጊዜና ድግግሞሽ) የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ ዓመታዊ የውስጥ ጥራት ኦዲት ተከናውኖ አብዛኛው የእርምት እርምጃ ተወስዷል ሌሎችም በመወስድ ላይ ይገኛሉ (ክንውን 100%)፡፡

5.2.3. አዳዲስ የንጽጽር ፕሮግራሞችን በግዝፈት፣ በግፊት እና በሚዛን የአለካክ መስኮች ለማፈላለግ እና ለማካሄድ ታቅዶ በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት እና በግፊት አለካክ መስኮች በተደረጉ የአህጉራዊ በየነ-መረብ ቴክኒካል ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተሳትፎ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም በኬሚካል ሥነ-ልክ በአካል በአህጉራዊ ቴክኒካል ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተሳትፈዋል (ክንውን 100%)፡፡

## 5.3 በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት (ክንውን 50%)፡፡

5.3.1 በወበቅ (Humidity) እና በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በወበቅ፣ እርጥበትና የኃይል የአለካክ መስኮች ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማስፋት ለጀርመንና ለኢትዮጵያ የዕውቅና ሰጪ ተቋማት ማመልከቻ ያቀረብን ቢሆንም ለጀርመን ዕውቅና ሰጪ ካቀረብናቸው የአለካክ መስኮች ወበቅና በውስጥ ላቦራቶር በመሆኑና እርጥበት በካሊብሬሽን ዘርፍ የሚመደብ ባለመሆኑ ማመልከቻው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ዕውቅና ሰጪ ተቋም ሁሉም ተቀባይነት አግኝቶ በሂደት ላይ ይገኛል (ክንውን 50%)፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት 'በግንባታ ላይ ያሉ ላቦራቶሮች በወቅቱ ባለመጠናቀቃቸው እና የአሮጌው ህንጻ ላቦራቶሮች የሚፈርሱ መሆናቸው በነባር ላቦራቶሮች የነበረን ዓለም አቀፍ ዕውቅና በጊዜያዊነት እንዲታገዱ መደረጉና በወበቅ እና በሌሎች የአለካክ መስኮች ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸውን ለማስፋት የያዝነው ዕቅድ ለጊዜው ለማሳካት አልተቻለም፡፡

5.4. በ3 አለካክ መስኮች በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት (BIPM-KCDB)ማስመዝገብ (ክንውን 100%)፡፡

5.4.1. 'ኤሌክትሪካል፣ ሙቀት እና ይዘት የአለካክ መስኮችን በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ በክፍለ አህጉራዊ የሥነ-ልክ ድርጅት የጥራት ቴክኒካል ኮሚቴ /AFRIMETS TC-QS/ ለማስገምገም ታቅዶ 'በኤሌክትሪካል፣ ሙቀት እና ይዘት የአለካክ መስኮችን በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ በክፍለ አህጉራዊ የሥነ-ልክ ድርጅት የጥራት ቴክኒካል ኮሚቴ /AFRIMETS TC-QS/ ግምገማ ተደርጉ ተቀባይነት አግኝቷል (ክንውን 100%)፡፡

5.5. በአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት በመሳተፍ ስትራቴጂያዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ (ክንውን 100%)፡

5.5.1 ከዓለምአቀፍ (BIPM) ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ ለመሳተፍ ታቅዶ እ.ኤ.አ ከህዳር 15 - 18/2022 በፈረንሳይ በተካሄደው ዓለም ዓቀፉ የስነ ልክ ድርጅት 27ኛ ጠቅላላ ጉባዔ (CGPM) ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ ከተሳትፎውም ኢንስቲትዩታችንን የጥናትና ምርምር ማንዴቱን ለመወጣት የሚያስችሉትን ስትራቴጂዎች ለማስቀመጥ የሚረዱ ልምዶችን ለመቅሰም ተሞክሯል፡፡ እ.ኤ.አ ከሃምሌ 20 -21/2022 በድረገጽ አማካኝነት በተካሄደው የአፍሪካ ስነ-ልክ ድርጅትና ጎን ለጎን በተካሄደው ሀገራችን በተካተተችበት የስነ-ልክ ክፍለ አህጉራዊ ድርጅት በሆነው NEWMET ዓመታዊ ስብሰባዎች ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ በስብሰባዎቹም ኢንስቲትዩታችን ኢንስቲትዩታችን በዓለም ዓቀፉ የስነ-ልክ ተቋም የልኬት አቅም ዱታ ቤዝ ውስጥ እንዲመዘገቡለት የሚፈልጋቸውን የአለካክ ወሰኖች ሂደትን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ ኮሚኒኬሽኖች ተደርገው ውጤት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የኢንስቲትዩታችን ባለሙያዎች አባል በሆኑባቸው የቴክኒክ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ላይ የተቋማችንን ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተሳትፎዎች አድርገዋል ( ክንውን 100%)፡፡

5.5.2 በአህጉራዊ AFRIMETእና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባዎች ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት እና በግፊት አለካክ መስኮች በተደረጉ የአህጉራዊ በየነ-መረብ ቴክኒካል ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተሳትፎ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም በኬሚካል ሥነ-ልክ በአካል በአህጉራዊ ቴክኒካል ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተሳትፈዋል (ክንውን 100%)፡፡

**5.6 የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** ( ክንውን 73%)

5.6.1. በ 4 የስራ ሂደቶች (በሳ/መ/ስ/ም/ዳ/ት፣ በሳ/መ/ቴ/ም/ዳ/ት ፣በፋይናንስ ዳ/ት ፣ሰው ኃብት አስ. ዳ/ት (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ የሰነድ ዝግጅት ለማጠናቅቅ ታቅዶ ዶክመንቱን ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ተግባራዊ ማድረግ የሚቀር ይሆናል፡፡ (ክንውን 50%)

5.6.2. የሳይንስ መሳሪያዎች ፍኖተ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ የሳይንስ መሳሪያዎች ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 6. የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** (ክንውን 50%)፡፡

**6.1 የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ (ክንውን 50%)፡፡**

6.1.1 በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠናዎችን ማግኘት፣የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማጠናቀቅ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ 'ከ TECHIN በመጡ የ Frequenct counter generator መሳሪያዎች እና ከ ተቋሙ በመጡ ባለሙያዎች የካሊብሬሽን ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በሌላ በኩል በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠናዎች ስላልተገኘ ፣ የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀትም አልተቻለም የካሊብሬሽን አገልግሎትም ማስጀመር አልተቻለም (ክንውን 50%)፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት ምክንያት ስልጠና በመስኩ ባለመሰጠቱ እና የstandrad ዕቃ ግዥ ሂደቱ ባለመጠናቀቁ ነው፡፡

**ግብ 7 አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል** (ክንውን 79%)

**7.1 የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 87.8 %)

7.1.1 በተቋሙ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ሲስተሞችን (IFMIS, ICMIS፣EGPS) አጠናክሮ ለማስቀጠል ክትትል እና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በአገልገሎት ላይ ያሉ የIFMIS, ICMIS፣EGPS ላይ የተጠቃሚዎች አስተዳደር ስራዎች ፤የአካውንት አስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፎች በድምሩ 62 ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**7.1.2** የካሊብሬሽን እና የጥገና አልግሎት (አውቶሜት) E- service ኦላይን በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን ታቅዶ ለአገልግሎቱ እስፈላጊ የሆኑ የሆኑ ሶፍትዌሮች እንዲገዙ የስፔስፊኬሽን ዝግጅት ጀምሮ፤ የኢንሰታሌሽንና የኮንፊገሬሽን ስራዎች ሰርቨር ላይ ተሰርተዋል፡፡

- ለአገልግሎቱ የሚውሉ ሶፍትዌሮች( MET/CAL & MET/TEAM) በተቋሙ ሰርቨር እና የተጠቃሚዎች ኮምፒውተሮች ተጭነው የኢንስታሌሽንና የኮንፊገሬሽን ስራዎች ተሰርቷል፤

- የካብሬሽን ደንበኞች መረጃ ወደ ዳታ ቤዝ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ የደንበኞች አገልግሎትን ጨምሮ ሁለት ላብራቶሪዎች ተመርጠው የስራ ላይ ልምምድ እያደረጉ ይገኛል፡፡
- የጥገና አገልግሎትን አውቶሜሽን ሙከራ ለመጀመር VPN (የሁለት ግቢ ኔትወርክ የማገናኘት) አገልግሎት ለኢቲዮ ቴሌኮም ጋር በመሆን እየተሰራ ሳይት ሰርቬይ ተጠናቋል (ክንውን 100%)፡፡

**7.2 ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ** (ክንውን 100%)፡፡

7.2.1 አገልግሎት ክፍያ የዋጋ ተመን ሰነድ መከለስ እና ለገ/ሚ ለማቅረብ ታቅዶ ሰነዱ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ለበላይ ሃላፊ ቀርቧል (ክንውን 100%)፡፡

7.2.2 የሚጸድቁ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ሂደት ለመከታተል ታቅዶ በሚቋቋሚያ ደንቡ ዙሪያ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴር ጋር በቅርብ አብሮ በመስራት ረቂቅ ደንቡ ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲላክ ተደርጓል በፍትህ ሚንስቴርም በአካል በመገኘት ክትትል እየተደረገ ይገኛል (ክንውን 100%)፡፡

7.3. **የጥናት ምርምር እና መመሪያ ማዘጋጀት** (ክንውን 0%)

7.3.1 የጥናት እና ምርምር መመሪያ ማጸደቅ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ መመሪያው ተዘጋጅቶ ለማፀደቅ ለማኔጅመንቱ ቀርቧል (ክንውን 80%)፡፡

**7.4. የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዥ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም** (ክንውን 100%) ፡፡

7.4.1 በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ለማጠናቀቅ ታቅዶ በዓመታዊ የግዥ ዕቅድ መሠረት የሠራተኞች የደንብ ልብስ፣ የፅዳት እቃዎች፣ ICT equpment፣ ልዩ ልዩ ቶነሮች፣ የጥበቃ እና የፅዳት አገልግሎት ግዥ ብሔራዊ ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በ EGP ሲስተም ግዥ ተከናውኗል፡፡ የኮምፒውተር ጥገና በብሔራዊ ጨረታ ያልተገኘ ሲሆን የበርነር ግዥ እና Fire wall በዋጋ ማቅረቢያ ጨረታ ግዢው ባለመሳካቱ አልተከናወነም (ክንውን 100%)፡፡

**7.5 የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ (ክንውን 80%)፡፡**

7.5.1 በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ለማድረግ ታቅዶ ቆጠራው የተጠናቀቀ ሲሆን ንብረት የማስወገድ ስራ ይቀራል (ክንውን 80%)፡፡

**ግብ 8 ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** (ክንውን 71.8%)፡፡

**8.1 ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 29.5%)፡፡

8.1.1 ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ለሚመጡ 21 ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ለማካሄድ ታቅዶ

- ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የዩኒቨርስቲ የመጣ አንድ ተማሪ ለ45 ቀናት የተግባር ልምምድ አድርገዋል፡፡
- ከግል ኮሌጅ ለመጣ አንድ ተማሪ የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ተሰጥቷል፡፡
- ለሶስት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የፊዚክስ ላቦራቶሪ ተክኖሎጅስቶች የአንድ ወር የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከአዲስ አበባ ተግባረዕድ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ለመጡ 35 በላይ ለሆኑ ተማሪዎች በሙቀት ሥነ-ልክ ላይ የልምምድ ስልጠና ተሰጥተዋል፡፡ (ክንውን 23.8%)፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት ተማሪዎቹ በወቅቱ ባለመምጣታቸው ነው፡፡

**8.2 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት (ክንውን 100%)፡፡**

8.2.1. ከ5 አቻ የወጪ የሥነ ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነት ማደስ እና ተግባራዊነቱን ለመከታተል ታቅዶ በተደረጉ የትብብር ስምምነቶች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ሲሆኑ፤ ኢንስቲትዩቱ ከነዚህ አቻ ተቋማት በባለሙያዎች የትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የእርከን ተዋረድ ትስስር ተግባራቶቹን ስኬታማ ከማድረግ አኳያ ተጠቃሚ ሆኗል ፡፡

- ከጀርመን የሥነልክ ኢንስቲትዩቱ PTB ጋር በተደረገ ድጋፍ፡
  - ለአንድ ወንድ ባለሙያ ዓለም ዓቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት ከቱርክ ሥነልክ ጋር በሚያዘጋጁት ስልጠና ላይ የሁለት ወር ነጻ ስልጠና ተገኝቷል፡፡
  - አንድ ሴት የኬሚካል ስነልክ ባለሙያ ከደቡብ ሥነ-ልክ ኢንስትቲትዩት ነጻ የሁለት ሳምንት ስልጠና በመሳተፍ የአየር ጉዞ ትኬት ድጋፍ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡

**8.3 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት (ክንውን 100%)፡፡**

8.3.1 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት ታቅዶ ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የኦክስጅን ማምረቻ ፕላንት ለጤና ተቋማት እንዲገለገሉበት ደረጃ ዝግጅት ላይ የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የትብብር ማእቀፍ እና እቅድ ዝግጅት ላይ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በጋራ ሊተገበሯቸው የሚችሉት

የፕሮጀክት ሃሳቦች እንዲካተቱ ተደርጓል። የሁለቱ ሚኒስቴር መስሪያቤቶች ባስቀመጡት ዕቅድ መሰረት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ለማድረግ በቀጣይ ይሰራል (ክንውን 100%)።

**ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ** (ክንውን 95.5%)።

**9.1 የሰው ሀብት ልማት ማልማት** (ክንውን 95.3%) ።

9.1.1 ለ180 ሠራተኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በ Research Metedology, Change mgt ፣እስታቲክስ፣ ምስልና ድምፅ ቅንብር፣ ኮሚቴ ተኮ፣ የሴት ሠራተኞች ፎረም የመረጃ ነፃነት ህግና ተያያዥ ጉዳዮች፣ Training On Integrazation፣ EGP እና በሌሎችም የስልጠና አይነቶች በጠቅላላ ድምር 261(ወ=159, ሴ=102)ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል። በተጨማሪም በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት በአለም ባንክ ብድር Electrical resistance metrology on Resistance Bridge,Thermocouple and Furness, Fixed point temperature and Temperature enclosure ላይ 28(ወ=20, ሴ=8) ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 100%)።

9.1.2 ሁለተኛ እና ሦስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ለመስጠት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የመግቢያ ፈተና ላለፉ 3 (ወ=2 ለሁለተኛ ዲግሪ, ሴ=1 ለሶስተኛ ዲግሪ) ሠራተኞች የት/ት ዕድል ተሰጥቷል (ክንውን 100%)።

**9.2 የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር** (ክንውን 96 %)።

9.2.1 ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሁለት ሕፃናት ብር21600 ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 20694 ብር ድጋፊ ተደርጓል (ክንውን 95.8%)።

9.2.2 ዝቅተኛ የደሞዝ ተከፋይ የሆኑ ሴቶችና ወጣት ሠራተኞችን ፕሮጀክት በመንደፍ ገቢያቸዉን እንዲያሳድጉ ለማመቻቸት ታቅዶ በኮተቤ ግቢ የጓሮ አትክልት የማልማት ሥራዎች ተሰርተው ዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ የሆኑ ሴቶችና ወጣት ሠራተኞች የዕድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል (ክንውን 100%)።

**9.3 የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 91.6%)።

9.3.1. በተቋም የሚገኙ የስራ ክፍሎችን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት መለየት፣ ደረጃ መስጠት እና ለተቋሙ ይፋ ለማድረግ እና መከታተል ታቅዶ በግዥ ፣ በሰው ሀብት ቅጥር ፣

በነዳጅ አጠቀቃም እና በካሊብሬሽን አሰጣጥ ዙሪያ የመለየት ስራ ተሰርቷል (ክንውን 100%) ፡፡

9.3.2 በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በካሊብሬሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጥናት ተካሂዷል (ክንውን 100%) ፡፡

**ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል** (ክንውን 59.4%)፡፡

**10.1. የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ** (ክንውን 56.3%)፡፡

10.1.1 የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር /SSDL/ የ X-ray machine እና የ Cs-137 Gamma source shutter ብልሽት ተከታትሎ በማስጠገን እንደገና አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ የ X-ray machine እና የ Cs-137 Gamma source shutter ብልሽት ተከታትሎ እንደገና ለማስጀመር Display ተጠይቆ ተገዝቶዋል ችግሩን ለመለየት ሥራ ተጀምራዋል (ክንውን 50%)፡፡

**10.2. ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት** (ክንውን 100%)፡፡

**10.2.1.** ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ የቢሮ ቁልፍ ጥገና፣ የውጭና የውስጥ መብራት ጥገና፣ የመፀዳጃ ቤት ክትትልና ጥገና፣ የጣራ ጉረንዳዩ ማጽዳት ሥራ፣ ቁፋሮና የአረም ማጽዳት ሥራ፣ የቦሎ ፣ የመኪና ጥገና፣ የስልክ መስመር፣ የውሃ መስመር ጥገና ድጋፍና ክትትል ሥራ ተከናውኗል (ክንውን 100%)፡፡

**10.3. የሰው ሀይል ማሟላት (ክንውን 0%)፡፡**

10.3.1 በፀደቀው መዋቅር መሰረት ድልድል ለማካሄድ ታቅዶ አልተከናወነም (ክንውን 0%)፡፡ ያልተከናወነበት ምክንያት ደንቡ ስላልፀደቀ ነው፡፡

**10.4. የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ** (ክንውን 100%)፡፡

10.4.1 በተቋሙ ያሉ መሰረተ ልማቶችን ማስተዳደርና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ታቅዶ በአገልግሎት ላይ ላለው የIFMIS, ICMIS፣EGPS እና official email ላይ የተሰሩት የማስተዳደርና ደህንነት የመጠበቅ ስራዎች በተያዘው በጀት ዓመት ለ IFMIS, 15 የተጠቃሚዎች አስተዳደር ስራ፤ የ EGP ለሁሉም የስራ ሂደቶች ሀላፊዎችና ፅኃፊዎች ፣ ግዢ አጽዳቂ ኮሚቴዎች፤ የቴክኒካል ኮሚቴዎች የራሳቸው አካውንት እንዲኖራቸው እና መጠቀም እንዲችሉ በድምሩ 82 የተጠቃሚዎች አስተዳደር ስራ ተሰርቶ የአጠቃቀም ቴክኒክ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለሁሉም የስራ አመራር አባላትና ለክልል ተወካዮች እንዲሁም ለተቋሙ መረጃ መስጫና መቀበያ የሚያገለግሉ በድምሩ 44 ኦፊሺያል ኢሜል ተፈጥሮ የአጠቃቀም ቴክኒክ ድጋፍ ለጠየቁ 25 ተጠቃሚዎች ድጋፍ

ተደርጓል ። ዲጂታላይዜሽንን እውን ለማድረግ ከደንበኞች ጋር ግንኙነት ላላቸው ባለሙያዎች የተቋሙ ህጋዊ ኢሚል መጠቀም እንዲችሉ ተጨማሪ የኢሜል አገልግሎት ለኢትዮ ቴሌኮም ተልኳል (ክንውን 100%)።

10.5. **የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት** (ክንውን 50%) ።

10.5.1. በዜጎች ቻርተር መሠረት አገልግሎት መሰጠቱን የትንተና ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በዜጎች ቻርተር መሠረት አገልግሎት መሰጠቱን የትንተና ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ሰነዱ ተዘጋጅቷል (ክንውን 100%) ።

**ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** (ክንውን 100%) ።

11.1. ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ (ክንውን 100%)

11.1.1. ኘሮጀክቶችን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ፡-

- በዓለም ባንክ ብድር በብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት የሚፈጸሙ የሥነ-ልክ ላቦራቶር መሳሪያዎች ፣ የወርክሾ መሳሪያዎች እና የስልጠና ግዥ ክንዉን ክትትልና ሪፖርት ዝግጅት፣
- በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ድጋፍ የተገኙ ስልጠናዎች ውጤታማነትን ለማረጋገጥ፣
- ብሎክ 8 የመካኒካል ላብራቶር ህንፃ ግንባታ ተጠናቆ መሣሪያዎች ወደ አዲሱ ህንፃ እየተጓጓዙ ስለመሆኑ
- የኬሚካል ላብራቶር እቃዎች በከፊል በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት በዓለም ባንክ ብድር ለማሟላት ጥያቄ ቀርቦ በሂደት ላይ ነው። ሌሎቹ ለማሟላት ለገንዘብ ሚ/ር የበጀት ጥያቄ ቀርቧል (ክንውን 100%)

11.2. **የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** (ክንውን 100%) ።

11.2.1 የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ማዘጋጀት ፣በየደረጃው መፈራረም እና የዉጤት ተኮር ምዘና ለማካሄድ ታቅዶ የ2015 በጀት ዓመት የ6 ወር ውጤት ተኮር ምዘና ተካሂዷል

- በጣም ከፍተኛ 37 (ወ=26, ሴ=11) ሠራተኞች
- ከፍተኛ 85 (ወ=49 ሴ=36) ሠራተኞች፤
- መካከለኛ 5(ወ=3, ሴ=2) ሠራተኞች፤
- ዝቅተኛ 1 (ወ=1) ሠራተኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሲሆን በአጠቃላይ 128 ሠራተኞች (ወ=79 ሴ=49) ምዘና ተጠናቋል (ክንውን 100%)።

## 4. የዋና ዋና ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎን

**ጠንካራ ጐን**

- በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ በኤሌክትሪካል አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት መጀመሩ
- በግዝፈት፣በኤሌክትሪካልና በግፊት የአለካክ መስኮች የእርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ መቻሉ
- በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የማማከር እና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶች መሰጠቱ
- በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ በዕቅዱ መሰረት የስልጠና አገልግሎት
- መሰጠቱ
- የአገልግሎት ገቢ አፈጻጸም
- ዕዉቅና በተገኘባቸዉ እና ባልተገኘባቸው የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት መከናወኑ
- (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ የሰነድ ዝግጅት መጠናቀቁ
- ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ በቨርቹዋል ተሳትፎ መደረጉ
- ለሶስት ሠራተኞች ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የት/ት ዕድል መሰጠቱ

**ደካማ ጐን**

- የክትባት መድኃኒቶች ማቆያ ፍሪጅ በማሻሻል ፕሮቶታይፕ ማምረት አለመቻሉ
- የግላስ ብሎዊንግ ወርክሾፕ ስራ ለማስጀመር ስልጠና እና ግዢ ማጠናቀቅ አለመቻሉ
- የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ጥገናና ኮሚሽኒንግ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑ
- በሙቀት አለካክ (thermometers, moisture) መስክ ካሊብሬሽን መጀመር አለመቻሉ
- በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች በ 'RPM calibration ,frequency counter and generator' ስልጠናዎችን ማግኘት፣የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማጠናቀቅ የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር አለመቻሉ
- በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ /photometer and radiometer/ የአለካክ መስኮች ስልጠናዎችን ማግኘት እና የካሊብሬሽን አገልግሎት ማስጀመር አለመቻሉ

- በኬሚካል የሥነ-ልክ መስክ  የካሊብሬሽን አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል በ 'Gas Metrology' በ 'Inorganic chemistry'  በ 'Organic chemistry'  በ 'PH measurement and related' ስልጠናዎች ማግኘት አለመቻሉ
- የጥናት  እና  ምርምር መመሪያ ማጸደቅ አለመቻሉ
- የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር /SSDL/ የ X-ray machine እና የ Cs-137 Gamma source shutter ብልሽት ተከታትሎ በማስጠገን  አገልግሎት አለመጀመሩ
- ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶች አለመወገዳቸው
- ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ
- ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የትብብር ስምምነት አለመታደሱ
- በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ አለመከናወኑ
- በፀደቀው መዋቅር መሰረት ድልድል ማካሄድ አለመከናወኑ

## 5. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

### ያጋጠሙ ችግሮች

- የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩ
- በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት እየተገነቡ ያሉ ህንጻዎች የግንባታ ሥራ መጓተት
- የበጀት እጥረት ማጋጠሙ

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ተሽከርካሪ ለማግኘት  በገንዘብ ሚ/ር ክትትል እየተደረገ ነው
- ከን/ቀ/ት/ሚኒስቴር ጋር በመሆን የቅርብ ክትትል ማድረግ
- ከገንዘብ ሚ/ር ጋር በቅርበት በመከታተል ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ ለመፍታት ተሞክሯል

## 6. የ2015 በጀት ዓመት የሰው ኃይል መረጃ ሪፖርት

| ተ.ቁ | የሠራተኞች የት/ደረጃ | በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ | | | አዲስ የተቀጠሩ | | | ከተቋሙ የለቀቁ | | | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | 1ኛ-12ኛ | 20 | 23 | 43 | - | - | - | - | - | - | 20 | 23 | 43 |
| 2 | TVT (Level) | 4 | 14 | 18 | - | - | - | - | - | - | 4 | 14 | 18 |
| 3 | ዲኘሎማ (10+3) | 5 | 17 | 22 | - | 1 | 1 | 1 | - | 1 | 4 | 18 | 22 |
| 4 | ቢ.ኤ/ቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 80 | 30 | 110 | - | - | - | - | - | - | 80 | 30 | 110 |
| 5 | ኤም.ኤ/ኤም.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 14 | 5 | 19 | - | - | - | - | - | - | 14 | 5 | 19 |
| 6 | ፒ.ኤች.ዲ | 2 | - | 2 | - | - | - | - | - | - | 2 | - | 2 |
| ድምር | | 125 | 89 | 214 | - | 1 | 1 | 1 | - | 1 | **124** | **90** | **214** |

**ማስታወሻ**

በኢቴኢ ከኳሊቲ ኢንጅነሪንግ ማዕከል ወደ በኢንስቲትዩታችን በጊዜያዊነት ተመድበው ከመጡ ሠራተኞች ዉስጥ ቋሚ ምደባ ያላገኙ ነገር ግን እየሠሩ ያሉትን 31(ወ=22, ሴ=9) ጨምሮ በአጠቃላይ በኢንስቲትዩታችን ሰራተኞች ብዛት 245(ወ=146, ሴ=99) ነዉ።

| 7. የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ | ከሐምሌ - ሰኔ ወር ላይ የዋለ /ወጪ | | ከ2015 በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ጋር ሲነጻጸር |
| | ከመንግስት | ከመንግስት | ከውጭ እርዳታ | |
| መደበኛ በጀት | | | | |
| ፕሮግራም 01 | 29,516,506.97 | 27297673.69 | | **92.5** |
| ፕሮግራም 02 | 6,817,279.17 | 6,368,176.28 | | **93.4** |
| **ፕሮግራም 03** | 13,930,799.64 | 13,400,998.87 | | **96.2** |
| ፕሮግራም 04 | 7,179,289.57 | 6,066,986.66 | | **84.5** |
| ንዑስ ድምር | 57,443,875.35 | 53,133,835.5 | | **92.5** |
| ካፒታል በጀት | | | | |
| ድምር | 57,443,875.35 | 53,133,835.5 | | **92.5** |

## 8. ማጠቃለያ

የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ከ2013-2017 ሊከናወን የተያዘውን የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት በማድረግ እና የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም እና ያልተጠናቀቁ ተግባራትን በማካተት በ11 ግቦች፤ በዋና ዋና እና ዝርዝር ተግባራት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ተከልሶ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን ከዓለም አቀፍ ሥነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ስርዓትን ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ 259(ወ=157, ሴ=102) ሠራተኞችን ይዞ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ከማሳደግ አንጻር በተለያዩ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የህክምና መሳሪያዎች " Testing እና Verification " ሁኔታ ጥናት ማጠናቀቅ፣ በተመረጡ የጨርቃጨርቅና ቆዳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ላይ የተመጣጠነ ሚዛን ማስተካከያ ውጤት ወጥነት እና አስተማማኝነት ላይ ጥናት ማካሄድ፣Potentiometric Method' በመጠቀም የ 'Resistance' ልኬት ትክክለኛነት ማሻሻል፤ጥናቱ ተጠናቆ ሪፖርት ተዘጋጅቷል እንዲሁም በክትባት መድኃኒቶች ማቆያ ፍሪጅ በማሻሻል ፕሮቶታይፕ ማምረት በሂደት ላይ ነዉ፡፡
በተለያዩ የአለካክ መስኮች ለ 26873 የመለኪያ መሳሪያዎች የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ለ252 ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት እና ለ17 የህክምና መሳሪያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

በሥነልክ ዘርፍ ለአንሊሚትድ ፓኬጅንግ ድርጅት የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ፣ ለናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ ድርጅት ባለሙያዎች ISO 17025፡2017 የላቦራቶር ጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ላይ የጽንሰ ሃሳብ እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለሙያዎች አጠቃላይ በሥነ-ልክና እርግጠኛ ያለ-መሆን ጽንሰ ሀሳብ፣ በርዝመት፣በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በግፊት፣ በይዘት፣ በሚዛንና ኃይል መለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን፣ እንዲሁም የመለኪያ መሳሪያዎች አያያዝና ደህንነት አጠባበቅ ላይ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ በአናሎግ ኤሌክትሮኒክስ ላይ የህክምና ጥገና ባለሙያዎች ስልጠና እና በዲጂታል ኤሌክትሮኒክስ የዲዛይንና የብልሽት ፍለጋ (Design and Troubleshooting) ላይ ከህብረተስብ ጤና ኢንስቲትዩት ለተላኩ የባዮሜዲካል ምህንድስና ባለሙያዎች በላቦራቶሪ ተግባራዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን በተፈረመው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት በሳይንስ መሳሪያዎች አገልግሎቶችና ቴክኒካዊ ሥራዎች እና ህክምና መሳሪያዎች "Toubleshooting" ላይ ስልጠና በአዳማ ከተማ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በሥነልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የማማከር አገልግሎቶች ተሰጥቷል፡፡

ተደራሽነትን ከማሳደግ አንጻር በሥነልክ ዘርፍ የዉስጥ ካሊብሬሽን ለማቋቋም ለአንሊሚትድ ፓኬጂንግ ኢንደስትሪ እና ለኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን በሙቀት የመስክ ካሊብሬሽን ላይ የቴክኒክ ድጋፍ እና ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ለመለኪያ መሣሪያዎች ግዥ የቀረቡ ጨረታዎች የቴክኒክ ግምገማ ሪፖርት ላይ የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ተሰጥቷል፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ አክርድቴሽን አገልግሎት የጥራት ኦዲት ቴክኒካል ገምገማሚዎች /Technical Assessors/ የተግባር ስልጠና ሲሰጣቸው የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የላብራቶሪ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን እና ጥገና ተቋማዊ ማዕከል ለማቋቋም እንዲያስችልው አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችና ፋሲሊቲዎች ተጠንተው እንዲዘጋጁላቸው በጠይቁት መሰረት እየተሰራላቸው ይገኛል። በተጨማሪም በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎች ተዘጋጅቶ ዌብሳይት ላይ ተጭኗል። እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያዎች የተለያዩ መረጃዎች፣ ዜናዎች እና መልዕክቶች ተሠርተው ተሰራጭተዋል።

ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ከማሳደግ አንጻር ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች በተለያዩ የአለካክ ዘርፍ 214 መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ተከናውኗል። በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካልና በግፊት የአለካክ መስኮች የእርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል። ዕዉቅና በተገኘባቸው እና ዕውቅና ባልተገኘባቸው የውስጥ የጥራት ኦዲት ተከናውኗል። በዓለምአቀፍ (BIPM) በፈረንሳይ በተካሄደው የዓለም ዓቀፉ የሥነ ልክ ድርጅት 27ኛ ጠቅላላ ጉባዔ (CGPM) ላይ ተሳትፎ ተደርጓል። ከተሳትፎውም ኢንስቲትዩታችንን የጥናትና ምርምር ማንዴቱን ለመወጣት የሚያስችሉትን ስትራቴጂዎች ለማስቀመጥ የሚረዱ ልምዶችን ለመቅሰም ተሞክሯል። እ.ኤ.አ ከሃምሌ 20 -21/2022 በድረገጽ አማካኝነት በተካሄደው የአፍሪካ ስነ-ልክ ድርጅትና ጎን ለጎን በተካሄደው ሀገራችን በተካተተችበት የሥነ-ልክ ክፍለ አህጉራዊ ድርጅት በሆነው NEWMET ዓመታዊ ስብሰባዎች ላይ ተሳትፎ ተደርጓል። በስብሰባዎቹም ኢንስቲትዩታችን በዓለም ዓቀፉ የሥነ-ልክ ተቋም የልኬት አቅም ዴታ ቤዝ ውስጥ እንዲመዘገቡለት የሚፈልጋቸውን የአለካክ ወሰኖች ሂደትን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ ኮሚኒኬሽኖች ተደርገው ውጤት ተገኝቷል። በተጨማሪም የኢንስቲትዩታችን ባለሙያዎች አባል በሆኑባቸው የቴክኒክ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ላይ የተቋማችንን ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተሳትፎዎች አድርገዋል።
የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ በተመለከተ በኤሌክትሪካል፣ ሙቀት እና ይዘት የአለካክ መስኮችን በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ በክፍለ አህጉራዊ የሥነ-ልክ ድርጅት የጥራት ቴክኒካል ኮሚቴ /AFRIMETS TC-QS/ ግምገማ ተደርጉ ተቀባይነት አግኝቷል፣ በጊዜና ድግግሞሽ/Time and frequency/ አለካክ መስኮች የካሊብሬሽን አገልግሎት የተጀመረ ሲሆን በፎቶሜትሪና ራድዮሜትሪ የአለካክ መስኮች በመሳሪያዎቹ አቅራቢ ድርጅት በሚሰጠው ስልጠና ላይ 1 ሴት እና 6 ወንዶች በአጠቃላይ 7 የኢንስቲትዩት የሥነ-ልክ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።
የአሰራር ቅልጥፍናን ከማሻሻል አንጻር IFMIS፣ ICMIS እና e-GP ሲስተም ላይ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። ለካሊብሬሽን እና ለጥገና አገልግሎት ኦንላይን ለማድረግ የሚውል ፖርታልን

(E- service) ተግባራዊ ለማድረግ (Common Data center፣ Remote and mobility access፣ BSC; MET/CAL and MET/Team, E- learning,)፣ የስልጠና፣የቁሳቁስ ግዢዎች ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ፣ የሲስተም ልማት ግምገማዎች ፣ የግዥዎች ቴክኒክ ግምገማ ላይ ተሳትፎ በማድረግ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

የሠራተኛውን ብቃት ከማሳደግ አንጻር በተለያዩ ርዕሶች ላይ በውስጥ አቅምና በውጭ አሰልጣኝ በወ=159 ሴ=102 በድምሩ ለ261 ሰራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የመግቢያ ፈተና ላለፉ 3 (ወ=2 ለሁለተኛ ዲግሪ, ሴ=1 ለሶስተኛ ዲግሪ) የት/ት ዕድል ተሰጥቷል፡፡

የሴክተር ዘለል ተግባራትን በሚመለከት ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ የተቋሙ ሰራተኞች እና ወላጆቻቸውን ላጡ ሁለት ሕፃናት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ከደመወዛቸው ተቆራጭ በማድረግ 20694 ብር የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 11,699,973.53 የአገልግሎት ክፍያዎች ተሰብስቦ ለገ/ሚ ገቢ የተደረገ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት የተግባር አፈጻጸም 82% ሲሆን የበጀት አፈጻጸሙ 92% ሆኗል፡፡

## 9. የ 2015 በጀት ዓመት የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2014 መነሻ | የ2015 ዕቅድ ኢላማ | የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| ግብ 1 | የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ | | | | | |
| 1.1 | ጥናትና ምርምር ማካሄድ | | | | | |
| 1.1.1 | ጥናትና ምርምር ማካሄድ | 0 | 4 | 4 | 3.75 | 91.67 |
| 1.2 | የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.2.1 | የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | 25226 | 31065 | 31065 | 26873 | 86.51 |
| 1.3 | የጥገና አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.3.1 | የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት | 279 | 300 | 300 | 252 | 84 |
| 1.4 | የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.4.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ሙያዊ ስልጠና መስጠት | 0 | 8 | 8 | 8 | 100 |
| 1.5 | የምክር አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.5.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች 100% የምክር አገልግሎቶች መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6 | የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት | | | | | |
| 1.6.1 | የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት | 11 | 26 | 26 | 17 | 65.38 |
| 1.7 | የተጠቃሚ እርካታ መመዘን | | | | | |
| 1.7.1 | የደንበኞች እርካታ ላይ ጥናት ማካሄድ | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 2 | ተደራሽነትን ማሳደግ | | | | | |
| 2.1 | በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ አዳዲስ አገልግሎት መስጠት | | | | | |
| 2.1.1 | በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ በኤሌክትሪካል አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት መጀመር | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 2.2 | በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች አገልግሎት ወሰን ማስፋት | | | | | |
| 2.2.1 | በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ (thermometers, moisture) መስክ ካሊብሬሽን መጀመር | 0 | 2 | 2 | 1.6 | 80 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.3 | የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | | | | | |
| 2.3.1 | የጥገና ወርክሾፕ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.4 | የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆን ማድረግ | | | | | |
| 2.4.1 | ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ማዘጋጀትና መጫን | 4 | 12 | 12 | 100 | 100 |
| 2.5 | የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት | | | | | |
| 2.5.1 | በተመረጡ አካባቢዎች እና በዩኒቨርስቲዎች የግንዛቤማስጨበጫ መስጠት | 2 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| ግብ 3 | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | | | | | |
| 3.1 | የበጀት አጠቃቀምን መከታተል | | | | | |
| 3.1.1 | የፀደቀውን በጀት በእቅዱ መሰረት 100% መጠቀም | 86 | 100 | 100 | 89.35 | 89.35 |
| 3.2 | የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | | | | | |
| 3.2.1 | የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | 11 ሚሊዮን | 12 ሚሊዮን | 12 ሚሊዮን | 11,699,973.53 | 97.5 |
| 3.3 | የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል | | | | | |
| 3.3.1 | የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እና ክዋኔ ኦዲት ማዘጋጀት | 2 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| ግብ 4 | **የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት** | | | | | |
| 4.1. | **ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ ( ክብደት = 1 )** | | | | | |
| 4.1.1 | 1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ ማፈላለግ | 1 | 1 | 1 | 50 | 50 |
| ግብ 5 | አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ | | | | | |
| 5.1 | ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት | | | | | |
| 5.1.1. | በ4 (በዳይሜንሽናል፣ በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካልና በግፊት) የአለካክ መስኮች የመጀመርያ ደረጃ የአለካክ መስኮች ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ | 3 | 4 | **4** | 2 | 50 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.1.2 | 211 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት | 195 | 211 | **211** | 214 | 101 |
| 5.2 | ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል | | | | | |
| 5.2.1 | 5 (በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በይዘት እና ሚዛን) ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች ማስቀጠል | 5 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 5.2.2 | ዕዉቅና ባልተገኘባቸው 6 የአለካክ መስኮች (በዳይሜንሽናል፣ በሀይል፣ ይዘት (ላርጅ ቮልዩም) ፣ በቶርክ፣ በሀርድነስ፣ በጊዜና ድግግሞሽ) የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ መውሰድ | 4 | 6 | 6 | 6 | 100 |
| 5.2.3 | አዳዲስ የንጽጽር ፕሮግራሞችን በግዝፈት፣ በግፊት እና በሚዛን የአለካክ መስኮች ማፈላለግ እና ማካሄድ | 3 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| 5.3 | በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት | | | | | |
| 5.3.1 | በወበቅ (Humidity) እና በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት እና ዕውቅና ማስፋት | 0 | 2 | 2 | 1 | 50 |
| 5.4. | **በ3 አለካክ መስኮች በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት (BIPM-KCDB)ማስመዝገብ ( ክብደት = 1** | | | | | |
| 5.4.1. | ኤሌክትሪካል፣ ሙቀት እና ይዘት የአለካክ መስኮችን በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ በክፍለ አህጉራዊ የሥነ-ልክ ድርጅት የጥራት ቴክኒካል ኮሚቴ /AFRIMETS TC-QS/ ማስገምገም | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 5.5 | በአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት በመሳተፍ ስትራቴጂያዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ | | | | | |
| 5.5.1. | ከዓለምአቀፍ (BIPM) ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ | 1 | 1 | **1** | 1 | 100 |
| 5.5.2 | ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት | 0 | 2 | **1** | 1 | 100 |
| 5.6 | **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ ( ክብደት = 1.5)** | | | | | |
| 5.6.1. | በ 4 የስራ ሂደቶች (በሳ/መ/ስ/ም/ዳ/ት፣ በሳ/መ/ቴ/ም/ዳ/ት ፣በፋይናንስ ዳ/ት ፣ሰው ኃብት አስ. ዳ/ት (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ማድረግ | 0 | 1 | **1** | 0.7 | 73 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.6.2 | የሳይንስ መሣሪያዎች ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 6 | የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ | | | | | |
| 6.1 | የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ | | | | | |
| 6.1.1. | የአለካክ መስኮች/ወሰኖች ማሳደግ | 0 | 4 | 4 | 2 | 50 |
| ግብ 7 | አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል | | | | | |
| 7.1 | የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ | | | | | |
| 7.1.1 | በተቋሙ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ሲስተሞችን (IFMIS, ICMIS፣EGPS) አጠናክሮ ለማስቀጠል ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ | 2 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| 7.1.2 | የካሊብሬሽን እና የጥገና አልግሎት (አውቶሜት) E-service ኦላይን በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ማዘመን | 0 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 7.2 | ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ | | | | | |
| 7.2.1 | የአገልግሎት ክፍያ የዋጋ ተመን ሰነድ መከለስ እና ለገ/ሚ ማቅረብ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 7.2.2 | የሚጸድቁ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ሂደት መከታተል | 2 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 7.3 | **የጥናት ምርምር እና መመሪያ ማዘጋጀት ( ክብደት = 0.5)** | | | | | |
| 7.3.1 | የጥናት እና ምርምር መመሪያ ማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ | 0 | 1 | 1 | 0.8 | 80 |
| 7.4 | የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም | | | | | |
| 7.4.1. | በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ማጠናቀቅ | 2 | 2 | 1 | 1 | 100 |
| 7.5 | የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ | | | | | |
| 7.5.1. | በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 |
| ግብ 8. | ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል | | | | | |
| 8.1 | ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | | | | | |
| 8.1.1 | ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ለሚመጡ ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማካሄድ | 18 | 21 | 21 | 5 | 29.5 |
| 8.2. | ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8.2.1. | ከ5 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነት ማደስ እና ተግባራዊነቱን መከታተል | 3 | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 8.3. | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | | | | | |
| 8.3.1. | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | 2 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| ግብ 9 | የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ | | | | | |
| 9.1 | የሰው ሀብት ልማት ማልማት | | | | | |
| 9.1.1 | ለሠራተኞች ስልጠና መስጠት | 150 | 180 | 180 | 180 | 100 |
| 9.1.2 | ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት | 6 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| 9.2 | የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር | | | | | |
| 9.2.1 | ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሁለት ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ | 20964 | 21600 | 21600 | 20694 | 95.81 |
| 9.2.2. | ዝቅተኛ የደሞዝ ተከፋይ የሆኑ ሴቶችና ወጣት ሠራተኞችን ፕሮጀክት በመንደፍ ገቢያቸዉን እንዲያሳድጉ ማመቻቸት | | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 9.3 | የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ | | | | | |
| 9.3.1. | በተቋም የሚገኙ የስራ ክፍሎችን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት መለየት፣ ደረጃ መስጠት ፣ ለተቋሙ ይፋ ማድረግ እና መከታተል | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 9.3.2. | በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት ጥናት ማካሄድ | 0 | 1 | 1 | 0.9 | 90 |
| ግብ10. | የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል | | | | | |
| 10.1 | የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ | | | | | |
| 10.1.1. | የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር /SSDL/ የ X-ray machine እና የ Cs-137 Gamma source shutter ብልሽት ተከታትሎ በማስጠገን እንደገና አገልግሎት ማስጀመር | **0** | **2** | **2** | **1** | 50 |
| 10.2. | ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት | | | | | |
| 10.2.1 | ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ ፣ እድሳት እና የሰራተኛ መመገቢያ) | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10.3. | **የሰው ኃይል ማሟላት ( ክብደት = 3)** | | | | | |
| 10.3.1 | በፀደቀው መዋቅር መሰረት ድልድል ማካሄድ | 0 | 100 | 100 | 0 | 0 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10.4 | የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ | | | | | |
| 10.4.1. | በተቋሙ ያሉ መሰረተ ልማቶችን ማስተዳደርና ደህንነታቸውን መጠበቅ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 10.5 | **የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት （ክብደት = 2）** | | | | | |
| 10.5.1 | በዜጎች ቻርተር መሠረት አገልግሎት መሰጠቱን የትንተና ሰነድ ማዘጋጀት | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| **ግብ 11** | የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል | | | | | |
| 11.1 | ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | | | | | |
| 11.1.1 | ፕሮጀክቶችን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 4 | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 11.2 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም | | | | | |
| 11.2.1 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረም ፣ በየወሩ አፈጻጸም መገምገም እና ምዘና ማካሄድ | 3 | 3 | 3 | 3 | 100 |